# ኤችአይቪ/አመንምኔ

## ለጥያቄዎ መልስ

## (HIV/AIDS – Your questions answered)

July/ሐምሌ 2003

Amharic

**ኤችአይቪ/HIV አመንምኔ / AIDS**

ኤችአይቪ/ HIV የቀመው ለሰው የበሽታ መከላከል አቅም አዳካሚ ቫይረስ ይሆናል (Human Immunodeficiency Virus)። ኤችአይቪ HIV ለአመንምኔ/AIDS በሽታ ምክንያት ይሆናል።

**አመንምኔ / AIDS ምንድ'ነው?**

አመንምኔ/AIDS የቀመው ያልተለመደ የበሽታ መከላከል አቅም ድክመት ይሆናል (Aquired Immune Deficiency Syndrome)። Aquired ማለት ያልተለመደ ማለት ነው። Immunodeficiency ማለት የሰውነት በሽታ መከላከል ዘዴ መቋረጥ ማለት ነው። Syndrome ሲል ደግሞ ከሌሎች ጋር በተዛመደ በሽታዎች መጋፈጥ ማለት ነው። በዚህ አጋጣሚ የሰውነት በሽታ መከላከል አቅም ሲዳከም በሚጠቃበት ጊዜ የአመንምኔ/AIDS መፈጠር ይታወቃል።

**ኤችአይቪ/HIV እንዴት ይይዝዎታል?**

ኤችአይቪ/ HIV በሚከተሉት መንገድ ይተላለፋል፡

- ኤችአይቪ/ HIV ከያዘው ሰው ጋር ያለመከላከያ በሴት ብልት ወይም ፊንጢጣ ላይ ወሲብ ሲፈጽሙ
- ኤችአይቪ/ HIV ከያዘው ሰው ጋር የመርፌ መወጊያ መሳሪያ በመዋስ
- ኤችአይቪ/ HIV ከያዛት እናት በእርግዝና ወቀት፤ ሲወለድ፤ ወይም ጡት በማጥባት ወደ ህፃን ይተላለፋል።
- ኤችአይቪ/ HIV ከያዘው ሰው ጋር ያለመከላከያ በአፍ ወሲብ መፈጸም

በአውስትራሊያ ውስጥ ኤችአይቪ/ HIV ያለኮንዶም የግብረስጋ ግንኙነት በመፈጸምና የመውጊያ መርፌ መሳሪያ በመቀያየር በመተላለፍ የተለመደ ይሆናል።

**ከተባይ፤ እንስሳት፤ ከሽንት ቤት መቀመጫ፤ ከመተቃቀፍ፤ ከእጅ ሰላምታ፡ በቤት ባለ እቃ፤ በመዋኛ ገንዳና ወዘተ ኤችአይቪ/HIV ሊይዘን ይችላል ወይ?**

አይዝም! ኤችአይቪ/ HIV በመደበኛ ማህበራዊና ቤተሰባዊ ግንኙነት አይተላለፍም። ኤችአይቪ/ HIV ከሰውነት ውጭ ብዙ አይቀይም። ቫይረሱ በመደበኛ የቤት እቃ ማጠቢያ ወይም ሳሙና እንዲሁም የሞቀ ውሃ ሊሞት ይችላል።

**ጥንቃቄ ያለው ወሲብ ምን ማለት ነው?**

በጥንቃቄ ወሲብ መፈጸም ማለት የወንድ ዘር ፈሳሽ፤ ከሴት ብልት ፈሳሽ ወይም ደም በሁለት የወሲብ ጓደኞች ካልተላለፈ ይሆናል። በፊንጢጣ ወይም ሴት ብልት የግብረስጋ ግንኙነት ጊዜ ኮንዶም በአግባቡ መጠቀም የኤችአይቪ/ HIV የመተላለፍ ችግርን በጣም ይቀንሳል። ኮንዶም ሲጠቀሙ ብዙ ፈሳስ ማለስለሻ መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። እንዲሁም የሴት ኮንዶሞች ሲኖሩ ከፈሳስ ማለስለሻ ጋር መጠቀም ያስፈልጋል። በጋራ ሴጋ ማድረግ፤ መነካካት፤ መተቃቀፍ፤ ሰውነትን መተሻሸትና ስሜት ለመቀስቀስ መተሻሰት በጥንቃቄ ግብረስጋ ግንኙነት ውስጥ ይካተታሉ። ከወሲብ ጓደኛ አንደኛው ኤችአይቪ/ HIV ካለበት ወይም ለመኖሩ እርግጠኛ ካልሆኑ በጥንቃቄ ግብረስጋ ግንኙነት መፈጸሙ ይመረጣል። በኮንዶም ጥንቃቄ ያለው ግንኙነት መፈጸም ኤችአይቪ/ HIV ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተላላፊ በሽታዎችን (STIs) ለምሳሌ እንደ ጨብጥና ክላሚዲያ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል።

**በአፍ ወሲብ ኤችአይቪ/HIV ሊይዘን ይችላል ወይ?**

ያለመከላከያ የአፍ ወሲብ ግንኙነት ለኤችአይቪ/ HIV መተላለፍ ችግር አነስተኛ ሲሆን ኮንዶም አጥልቀ መፈጸም ወይም በአፍ ውስጥ አለማፍሰስ የሚመረጠው፡

- አንዳቸው ቁስልና ደም የሚያወጣ ድድ ካላቸው ወይም
- በቀጥታ ጥርስን ጠርጎ ከተጉምጠመጡ በኃላ።

**አጥብቀ መሳሳም ለኤችአይቪ/HIV መተላለፊያ መንገድ ነው ወይ?**

ይህ ምንም የማያሰጋ ተግባር ነው። በኤችአይቪ/ HIV የተያዙ ሰዎች በምራቃቸው ውስጥ በጣም አነስተኛ ቫይረስ ብቻ ስለሚገኝ ነው። የኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ በምራቅ ለመተላለፍ ብዙ ምራቅ በቆሰለ ቆዳ ወይም በሚደማ ድድ ውስጥ ወደ ደም ከገባ ይሆናል።

**የሌላ ሰው ደም በመውሰድ በኤችአይቪ/HIV መያዝ ችግር ምን ያህል ነው?**

በአውስትራሊያ ውስጥ ከግንቦት/May 1985 ጀምሮ ደም ለጋሾች የኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ ምርመራ እያደረጉ ናቸው። ይህ ማለት በአሁን ጊዜ ደም በማስተላለፍ የሚያስከትለወ ኤችአይቪ/ HIV ችግር በጣም አነስተኛ ነው።

**በኤችአይቪ/HIV ከተያዘ ሰው የደም እርዳታ ማግኘት እችላለሁ?**

አያገኙም – መርፌ፤ ማሽኒያ፤ መቧጠጫና የጣት መቀንጠጫዎች እንደገና ጥቅም ላይ አይውሉም።

**የኤችአይቪ/HIV ምልከቶች ምንድ'ናቸው?**

የኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ ምልከት ብዙ

Department of Human Services

Victoria
The Place To Be

ዓይነት ህመም ያሳያል። ኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ አለብኝ ብለው ካሰቡ ወይም ከዚሕ በታች ያለው ማኛውም ምልክት [ከአንድ በላይ ምልክቶች] ከታየ ሃኪምዎን ማማከር ያስፈልጋል።
ከኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ ጋር የተዛመዱ የህመም ምልክቶች እንደሚከተለው የተለመደ ይሆናል፡
- እንፍሎዌንዛ መሰል የበሽታ ምልክት
- ከባድና የማያቋርጥ የድካም ስሜት
- ትኩሳት፣ ብርድና በማታ ማላብ
- በፍጥነት ከብደት መቀነስ
- በአንገት ላይ፣ በብብት ስር ወይም በብሽሽት አካባቢ ያበጠ እጢ
- በአፍ አካባቢ ነጭ ነጠብጣብ ወይም በአፍ ውስጥ ያልተለመደ ምልክት
- በቆዳ ላይ ምልክት ወይም እብጠት [የማያምና ሃምራዊ ያደገ ወይም ጠፍጣፋ]
- ያለማቋረጥ መሳል ወይም ደረቅ ሳል
- ተቅማጥ
- የምግብ ፍላጎት መቀነስ

የኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ ያለበት ምንም ዓይነት የበሽታ ምልክት ላያሳይ ይችላል ነገር ግን የቫይረሱ ተሸካሚ ስለሆኑ በደም ወይም ከሰውነት በሚወጣ ፈሳሽ ወደ ሌላ ሰው ማስተላለፍ ይችላሉ።

**የኤችአይቪ/HIV ምርመራ ማግኘት እችላለሁ ወይ?**

አዎ፣ የኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ ለመኖሩ በደም ምርመራ ይታወቃል። ለኤችአይቪ/ HIV ተጋልጫለሁ ብለው ካሰቡ ሃኪምዎን ማየት ወይም በዝርዝሩ ውስጥ ባሉት አገልግሎት መሄድ።
የኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ በደም ውስጥ ከተገኘ ይህ ሰው HIV positive ያለው ይባላል።
አንድ ሰው በኤችአይቪ/ HIV ከተያዘ በኃላ ለአጭር ጊዜ ቫይረስ እንዳለበት አይታወቀም። ስለዚህ ከሶስት ወር በኃላ የደም ምርመራ እንደሚያስፈልግ ነው። የኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ የደም ምርመራ የሚያደርግ ሰው ሁሉ የቅድሚያና ድህረ ምርመራ መማከር ማግኘት ይኖርባቸዋል።

**የኤችአይቪ/HIV ምርመራ የሚያካትተው ምንድ'ነው?**

- ምርመራው የሚካሄደው በፈቃደኝነትና ከተስማሙ ብቻ ይሆናል።
- በምርመራው ስለሚካሄደው ማብራሪያ መቀረብ አለበት።
- ውይይቱ ስለ ምርመራው ለምን እንደሆነ መሆን አለበት።
- ከምርመራው በፊት መማከርት የሆነ ውጤት ይምጣ ከምርመራ በፊት ምክር መስጠት አስፈላጊ ይሆናል።

በምርመራ ውጤት ቫይረሱ ከተገኘ በድህረ መማከርት በኩል የስነልቦና ድጋፍ፣ በበለጠ ስለበሽታው ማብራሪያ እንዲሁም እርዳታ ወደሚሰጡ አገልግሎቶች መላክ ይሆናል። በምርመራ ውጤት ቫይረሱ ካልተገኘ በድህረ መማከርት በኩል ስለ ኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ የመከላከያ መልእክት መግለጫ ይሰጣል።

**ኤችአይቪ/HIV ከአመንምኔ/AIDS እንዴት ይለያል?**

**ኤችአይቪ/HIV ለአመንምኔ/AIDS መንስኤ ይሆናል።**
ኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ ያለበት ሰው አመንምኔ/AIDS ላይኖረው ይችላል። ኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ የሰውነት በሽታ መከላከያ አቅምን በማዳከም ለብዙ በሽታዎችና ነቀርሳ እንዲጋለጡ ያደርጋል። ለብዛኛው ኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ ያላቸው ሰዎች ችግሩ ወደ አመንምኔ/AIDS በሽታ ለመቀየር ብዙ ዓመታት ይወስዳል። ኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ ተሸካሚ የሆኑ ያለህክምና አልፎ አልፎ በመታመም ወደ አመንምኔ/AIDS በሽታ ለመቀየር ከ5 እስከ 10 ዓመታት ሊወስድ ይችላል። ይሁን እንጂ ከመቶ በጥቂት የሚቆጠሩ ሰዎች ከ10 ዓመት በኃላም በጤንነታቸው ምንም ችግር አይፈጠርም።
የአመንምኔ/AIDS በሽታን ለማግኘት ለየት ያለ የላቦራቶር ምርመራዎች ያስፈልጋል።

**ኤችአይቪ/HIV - አመንምኔ/AIDS መዳን ወይም መታከም ይቻላል ወይ?**

በአሁን ጊዜ ለኤችአይቪ/ HIV ቫይረስ ወይም ለአመንምኔ/AIDS በሽታ ከትባት ወይም ፈዋሽ አልተገኘለትም። ይሁን እንጂ ከኤችአይቪ/ HIV የተዛመደን በሽታ ለመከላከልና ወደ አመንምኔ/AIDS በሽታ እንዳይለወጥ የሚያዘገዩ መድሃኒቶች አሉ። እነዚህን መድሃኒቶች መውሰድ ቀላል አይደለም ምክንያቱም የሚያስከትሉት ተፅእኖ ስላላቸውና የመድሃኒት አወሳሰዱ አስቸጋሪ ስለሚሆን ነው። አንድ ሰው ለኤችአይቪ/ HIV መድሃኒቶችን መውሰድ ከጀመረ እስከ ህይወት መጨረሻ ድረስ መውሰድ አለበት። እንዲሁም ከኤችአይቪ/ HIV/ አመንምኔ/AIDS በሽታ ጋር በተያያዘ ለብዙዎቹ ህመም የመድሃኒት ህክምና እንደሚኖራቸው ነው።
እንዲሁም የተሟላ ህክምና በማድረግ በመድሃኒት የሚመጣውን ተፅእኖ/ችግር በመቆጣጠር ደህንነትን ማሻሻል ይቻላል። አዳዲስ መድሃኒቶችና ህክምናዎች ሁልጊዜ ይሞከራል።

**ለበለጠ ማብራሪያ**

Melbourne Sexual Health Centre, Carlton
**ስልክ ቁጥር** : (03) 9347 0244
**ለማይሰማ ጥሪ** TYY : (03) 9347 8619
**ለገጠር ጥሪ** : 1800 032 017
**ጥሪው በነፃና ምስጢራዊ ይሆናል**

**ለሞላው አስተዳደር ግዛት አገልግሎት፡**

AIDSLINE- 9347 6099
**ከከተማ ውጭ ጥሪ** : 1800 133 392
TYY : (1800 032 665
Victoria AIDS Council/ Gay Men's Health Centre: 9865 6700
**በነፃ ለመደወል**: 1800 134 840
TYY : (03) 9827 3733
Access Information Centre/**የመረጃ አቅርቦት ማእከል**: 9276 6993

www.accessinfo.org.au

The Centre Clinics/**የክሊኒኮች ማእከል፡**
Northcote Community Centre- 9481 7155
St Kilda- 9525 5866

Family Planning Victoria- 9257 0100

Action Centre- 9654 4766

**Rular STI Clinics/በገጠር የተላላፊ በሽታ ክሊኒኮች፡**
The Annexe Sexual Health Clinic, Ballarat- (03) 5333 1635
STD Clinic- Community Health Bendigo- (03) 5434 4330
Geelong Sexual Health Clinic- (03) 5221 4735
STD Clinic- Vermont Street Clinic, Wodonga- (03) 6051 7470
STD Clinic- Latrobe Regional Hospital, Traralgon- (03) 5173 8000